የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር [illegible]/5/308
No
ቀን 23/02/2011
Date

ለወ/ሮ ፋጡማ ሐምዱ

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>

እርስዎ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ማቅረብዎ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው አይደለም በማለት የሰጠውን የውሳኔ ግልባጭ 6/ስድስት/ ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ ሰጥተንዎታል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ኬሪያ ኢብራሂም አሊ
የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ

<u>ግልባጭ</u>

- ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉደዮች አጣሪ ጉባኤ
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
  <u>በፌዴሬሽን ምክር ቤት</u>

ስልክ 223322 Tel. 242301/03
ፋክስ 242304 Fax 241208
E-mail: holethiopia@gmail.com
Web Site: http://www.hofethiopia.gove.et
ፖ.ሣ.ቁ. 20212/1000 P.O.Box
አዲስ አበባ Addis Ababa

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

## 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

**መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም**

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋጡማ ሐምዱ

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ሁሴን ቱፋ (2 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2008 ዓ.ም ለጉባኤው ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ ከጋብቻ ንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ የተደረገ ክርክርን የተመለከተ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው 2ኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት የጋብቻ ንብረት ክፍፍል ክስ ሲሆን አመልካች 1ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን፣ ሌላኛዋ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ አረቤ ጉደቶ 2ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን እንደዚሁም ሌላ አንድ ግለሰብ 3ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን በሊሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍ/ቤት በተደረገ ክርክር ነው፡፡

የቀረበለትን ክርክር በመጀመሪያ የተመለከተው የሊሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከተመለከተ በኋላ አዋሣኛቸው ተጠቅሶ በተለያየ ቦታ ከሚገኙ በጥቅሉ 15½ /አስራ አምስት ተኩል/ ሄክታር መሬት ውስጥ አመልካች የግሌ ነው ሲሉ ክርክር ያቀረቡበትን 4 ሄክታር መሬት ከ1982 ዓ.ም በፊት ለአመልካች የተሰጠ እና በ1982 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡን በመጥቀስ ይህ 4 ሄክታር ይዞታ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ቀሪው 11 ሄክታር መሬት በ1982 ዓ.ም በሕጋዊ መንገድ ተለክቶ ሲሰጥ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የነበሩ እና እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን በምስክሮች ቃል እና ከወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በተላከው ማስረጃ ማረጋገጡን በመጥቀስ ይዞታውን አመልካች፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ለ3 ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በመዝገቡ ላይ 2ኛ ጣልቃ ገብ የሆኑት ሌላኛዋ ሶስተኛ ሚስት ከ1992 ዓ.ም በኋላ መጥተው ከ11 ሄክታሩ ላይ ሊካፈሉ እንደማይችሉ በመጥቀስ ከ1ኛ ተጠሪ ድርሻ ላይ ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በአከራካሪነት በቀረቡት

ክብቶች ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች የእገሌ የግል ነው በሚል ለይተው አለመመስከራቸውን በመግለፅ 3ቱ ሚስቶች እና 1ኛ ተጠሪ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በመጨረሻ በበቆጂ ከተማ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት በተመለከተ 3ኛ ጣልቃ ገብ የሆነው ግለሰብ ቤቱ ያረፈበትን ይዞታ በስጦታ ስለማግኘቱ እና በራሱ ገንዘብ ቤቱን ስለመስራቱ አላስረዳም በማለት መብት የለውም ካለ በኋላ በሌላ በኩል አመልካች፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እኩል የመካፈል መብት ያላቸው መሆኑን በምስክሮች ያረጋገጠ መሆኑን ጠቅሶ በተጨማሪ 2ኛ ጣልቃ ገብ (ወ/ሮ አረቤ ጉደቶ) ከ1ኛ ተጠሪ ድርሻ ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በውሣኔው ላይ በስር ፍ/ቤት በ2ኛ እና 3ኛ ጣልቃ ገቦች ይግባኝ የቀረበለት የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ በአከራካሪው የመሬት ይዞታ ላይ ሁሉም ሚስቶች እየተጠቀሙበት በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ እና ሁሉም ሚስቶች እኩል ይካፈሉ በማለት ቀሪ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማፅናት ወስኗል፡፡

በከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ በአሁን አመልካች፣ በአሁን 2ኛ ተጠሪ እንደዚሁም 3ኛ ሚስት በሆኑት ወ/ሮ አረቤ ጉደቶ የቀረበለትን ይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሁሉንም ወገን ክርክር ከሰማ በኋላ በተጨማሪም ከሚመለከተው የመንግስት አካል ማስረጃ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በውሳኔውም ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ለየብቻቸው ይዘው የሚገኙትን ይዞታ ለማጣራት ባደረገው ጥረት 1ኛ ተጠሪ ከሦስተኛ ሚስታቸው ጋር (ከወ/ሮ አረቤ ጉደቶ ጋር) 4.0418 ሄክታር ለብቻቸው መያዛቸውን እንደዚሁም 2ኛ ተጠሪ 2.3575 ሄክታር ይዞታ ለብቻቸው ይዘው የቆዩ መሆኑን በመለየት በአንጻሩ አመልካች ለብዙ ጊዜ ግብር እየከፈሉ እየተጠቀሙበት ከቆየው 4 ሄክታር ውስጥ የብቻቸው 2.3468 ሄክታር መሆኑን በማረጋገጥ በሌላ በኩል 3ቱም ሚስቶች እንደዚሁም ከ2ኛ ተጠሪ የሚወለዱ ሁለት ልጆች የሚኖሩበትን የመኖሪያ ቤት ይዞታ ጠቅላላ ስፋቱ 5.8723 ሄክታር መሆኑን በመጥቀስ ከዚህ ውስጥ የአመልካች ድርሻ 1.6532 መሆኑን በመለየት እነዚህ ይዞታዎች ለአመልካች የሚገቡ ናቸው ብሏል፡፡ በመቀጠልም ከላይ እንደተጠቀሰው 2ኛ ተጠሪ 2.3575 ሄክታር የሆነ ይዞታ ለብቻቸው ይዘው እንደሚገኙ መረጋገጡን በመጥቀስ ከዚህ ይዞታ በተጨማሪ ከላይ በመኖሪያ ቤት ይዞታነት ከተለየው ጠቅላላ ይዞታ ውስጥ ከላይ የተጠቀሰው የአመልካች ድርሻ መጠን እንደዚሁም የ2ኛ ተጠሪ 2 ልጆች ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪ ይዞታውን ከአመልካች ውጪ ያሉ ሁለቱ ሚስቶች እና ባል (1ኛ ተጠሪ) እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በመቀጠልም በበቆጂ የሚገኘውን አንድ ቤት ከ10 ሰርቪስ ቤቶች ጋር ያለውን 3ኛ

ሚስት የሆኑት ወ/ሮ አረቤ ጉደቶ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከመጋባታቸው በፊት የተሰሩ በመሆኑ አመልካች፣ 1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ እኩል 1/3ኛ ድርሻ እንደሚኖራቸው በመጥቀስ ወ/ሮ አረቤ ጉደቶ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከተጋቡ በኋላ የተሰሩትን 5 ክፍል ቤቶች ሦስቱም ሚስቶች እና 1ኛ ተጠሪ እኩል 1/4ኛ ድርሻ ይኖራቸዋል ሲል ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ በአሁን 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች እንደዚሁም 3ኛ ሚስት በሆኑት ወ/ሮ አረቤ ጉደቶ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን አስቀርቦ ሶስት መዝገቦችን አጣምሮ ከመረመረ በኋላ አመልካች በስር በሊሙና ቢልቢሎ ወረዳ ፍ/ቤት ካቀረቡት አቤቱታ መረዳት የሚቻለው የአሁን 2ኛ ተጠሪ ክፍፍል ከጠየቁበት የመሬት ይዞታ ውስጥ 4 ሄክታር የሆነውን በመለየት የኔ ነው ሲሉ ከመጠየቅ በቀር የጠየቁት ዳኝነት ያልነበረ መሆኑን በመጥቀስ ለመካፈል ባልጠየቁት ይዞታና ሌሎች ንብረቶች ላይ እንዲካፈሉ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት አመልካች የጠየቁት 4 ሄክታር እንዲሰጣቸው መወሰኑን በመጥቀስ በቀሪ 11 ሄክታር ይዞታ ላይ ከአመልካች ውጪ ያሉት ሚስቶች እና 1ኛ ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በበቆጂ ከተማ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት በተመለከተ 3ኛ ሚስት የሆኑት ግለሰብ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከመጋባታቸው በፊት ተሰሩ የተባሉትን 10 ክፍል ቤቶች 1ኛ ተጠሪ እና 2ኛ ተጠሪ እኩል ይካፈሉ በማለት 3ኛዋ ሚስት ወደ ጋብቻው ከመጡ በኋላ ተሰሩ የተባሉትን 5 ክፍል ቤቶች ደግሞ የአሁን 1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች እንደዚሁም 3ኛዋ ሚስት እኩል ይካፈሉት ሲል ወስኗል፡፡ በተጨማሪ የሰበር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤት የተከራካሪዎች ልጆች ድርሻን አስመልክቶ የስር ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ ተጠቃሾቹ ልጆች ቀርበው ሳይከራከሩ የተሰጠ ነው በማለት እና ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

በጉዳዩ ላይ በአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አያስቀርብም ሲል ወስኗል፡፡

ከላይ በመጨረሻ ጸንቶ ባለው ውሳኔ ላይ አመልካች ለጉባዔው ያቀረቡት አቤቱታ ፍሬ ሃሣብ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ከ1954 ዓ.ም ጀምሮ በትዳር አብረን ስንኖር ከእኔ በኋላ 2ኛ ተጠሪን ጨምሮ ሁለት ሚስቶችን አግብቷል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በመፍረሱ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ያፈራሁትን መኖሪያ ቤት እና የግሌን የእርሻ መሬት በማካተት 2ኛ ተጠሪ ክፍፍል ያቀረቡ ሲሆን ስንከራከር ቆይተን በመጨረሻ 1ኛ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረበው ማመልከቻ አመልካች ባልጠየቀችው ዳኝነት ውሣኔ

ተሰጥቷል በማለት ክርክር ሳያቀርብ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህንን መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሣኔ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 35 የተሰጠኝን የንብረት ባለቤት የመሆን መብቴን ይጥሣል ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉባዔውም ጉዳዩን በጥልቀት እንደመረመረው በተያዘው ጉዳይ በፍ/ቤቶች ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መረዳት የሚቻለው የአሁን 1ኛ ተጠሪ አቶ ሁሴን ቱፋ በመጀመሪያ ከአመልካች ጋር ወይም ከወ/ሮ ፋጡማ ሐምዱ ጋር በመቀጠል በሁለተኛ ሚስትነት ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ወይም ከወ/ሮ ቢሹ ዋንፊሮ ጋር በመቀጠልም ከወ/ሮ አረቤ ጉደቶ ጋር በ3ኛ ሚስትነት ተጋብተው ለረጅም ጊዜ የኖሩ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህም መሰረት በዚህ ጉዳይ ላይ መመልከት እንደሚቻለው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች የግሌ የሆኑት 4 ሄክታር የሚሆኑ ይዞታዎች ከክርክሩ ይውጡልኝ ሲሉ ከመጠየቅ በቀር በቀሪ ንብረቶች ላይ ክፍፍል አልጠየቁም በሚል መነሻ አመልካችን ከሌሎች ንብረቶች ሁሉ ውጪ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ በአንድ በኩል አመልካች ጸንቶ ያለው ጋብቻቸው ሳይፈርስ የንብረት ክፍፍል እንዲጠይቁ የሚያስገድድ በመሆኑ ሕግን ያልተከተለ እና ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በሌላም በኩል በምክንያታዊ አስተሳሰብ አመልካች የግሌ የሚሉትን ይዞታ ከክርክሩ ይውጣልኝ ሲሉ ክርክር እያነሱ እያለ የጋራ ሊባሉ የሚችሉ ንብረቶችን በተመለከተ ክርክር አላነሱም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ አመልካችን ከሌሎች ንብረቶች በማግለል የሰጠው ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 35 ንኡስ አንቀጽ 7 የተደነገገውን የሴቶችን ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት የሚጋፋ ነው፡፡

ፍ/ቤቶች በፍቺ ተጠናቆ ክርክር ያስነሳውን ጋብቻ በተመለከተ ብቻ ከሌሎቹ ጸንተው ካሉት ጋብቻዎች አንጻር የንብረት ድርሻውን በንጽጽር በመለየት ላይ ብቻ በመመስረት መወሰን ሲገባቸው ጸንተው ያሉትን ጋብቻዎች የተጋቢዎች ድርሻ ጭምር በመለየት ወይም ክፍፍል በማድረግ መወሰናቸው ጸንተው ያሉትን ጋብቻዎች የማፍረስ ውጤት ያለው በመሆኑ ውሳኔው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34 ንኡስ አንቀጽ 3 የተመለከተውን ለቤተሰብ የተሰጠውን ከሕብረተሰብና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት የሚጋፋ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተሰጥቶ በፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ የሕገ መንግስት ጥሰት ያለው

በመሆኑ ውሳኔው ውድቅ ሆኖ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉን የቤተሰብ ሕግ ሕገ መንግስታዊነትን በተላበሰ መልኩ በመተርጎም አመልካች በሕግ አግባብ ከሌሎች ንብረቶች ጭምር የሚኖራቸው ድርሻ የሚኖር መሆን አለመሆኑን በመመርመር እንዲወስን ጉዳዩ ሊመለስለት የሚገባው ነው። በዚሁ አግባብ በመጨረሻ ጸንቶ ባለው ውሳኔ ላይ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልጋል ሲል ጉባኤው በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ ለመጨረሻ ውሳኔ ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲተላለፍ የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል።

ምክር ቤቱ በሕገመንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው ጉዳዩ ታይቶ እንዲያቀርብ በመምራት የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ባቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ሰፊ ውይይት በማድረግ ጉዳዩን መርምሮታል። በፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ተመርምሮ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ አመልካችን ከጋራ ንብረት ክፍፍል ውጪ ማድረጉ ሕግን የተከተለ አለመሆኑና ውሳኔው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መታረም ሲገባው አለመታረሙ አግባብ እንዳልሆነና ውሳኔው የሕገ መንግስት ጥሰት ያለበት ስለሆነ ውድቅ ሆኖ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉን የቤተሰብ ሕግ ሕገ መንግስታዊነት በተላበሰ መልኩ በመተርጎም አመልካች በሕግ አግባብ ከሌሎች ንብረቶች ጭምር የሚኖራቸው ድርሻ የሚኖር መሆን አለመሆኑን በመመርመር እንዲወስን ሊመለስለት ይገባል በሚል የሰበር ሰሚ ችሎቶች ውሳኔ ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ለመጨረሻ ውሳኔ ለምክር ቤት እንዲቀርብ የውሳኔ ሀሳብ መቅረቡን መገንዘብ ተችሏል።

ከዚህም በመነሳት አመልካች ከአቶ ሁሴን ቱፋ ጋር ያላቸው ጋብቻ ባልፈረሰበት ሁኔታ ከባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ውጪ ሆነዋል በማለት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35 ንኡስ አንቀጽ 7 የተረጋገጠው መብታቸው በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተጥሷል መባሉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም።

በሌላ በኩል አመልካች ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ሁኔታም ቢሆንም በጋራ ሀብታቸው ላይ ክርክር ሲነሳ የግል ሀብታቸውን ብቻ ለማስቀረት ከመከራከር በተጨማሪ ከጋራ ሀብቱ ላይ ያላቸውን መብት በመግለጽና በመለየት እንዲከበርላቸው ዳኝነት መጠየቅና መከራከር ሲገባቸው ባልጠየቁት ጉዳይ ላይ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ውሳኔ መስጠት ነበረበት ተብሎ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የመባሉን ሁኔታ ስንመለከት ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም።

በአጠቃላይ ጉዳዩ ሲታይ የፍሬ ነገር ክርክርን በማስረጃ አጣርቶና መዝኖ እንዲሁም ሕጎችን ተርጉሞ ውሳኔ የመስጠት ስልጣንና ሀላፊነት የፍርድ ቤቶች ስለሆነ በዚህ አግባብ ውሳኔ መስጠታቸው ከሕገ መንግስቱ ጋር የሚቃረን ባለመሆኑ ምክር ቤቱ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ወስኗል፡፡

<u>ትእዛዝ</u>

1. የውሳኔው ግልባጭ ለባለጉዳዩ ይሰጥ፡፡
2. የምክር ቤቱን ውሳኔ እንዲያውቀው ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ይላክ፡፡